የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በኒው ዮርክ
THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHDO CHURCH OF OUR SAVIOR INC. IN NEW YORK CITY

302 East 206 St Bronx, N.Y. 10467

**ለመላው የመድኃኔዓለም አባሎችና ወዳጆች ሁሉ ፣**

**ከሁለት ዓመታት በላይ በድንገት የወረረን በሽታ አስከተከሰተ ድረስ የመድኃኔዓለምን ክብረ በዓል በታላቅ ደስታና ዕልልታ እንዲሁም ከሩቅና ከቅርብ ከመጡ እንግዶች፥ ምዕመናንና ካህናት ጋር ሆነን ውብና ግርማ ባለው ቤተክርስቲያናችን በህብረት ስናከብር መቆየታችንን በትዝታ እናስታውሳለን። ይህ ወረርሽኝ የነጠቀብንን ልማድና አምልኮ ተረስቶ እንዳይቀር አንደ ድሮውም ባይሆን ሁኔታዎች በፈቀዱልን መጠን ከናንተና ከአካባቢያችን ቤተ ክርስትያን አባሎች ጋር በአንድነት ለማክበር በጌታችንና በመድኃኒታችን ፈቃድ ተነሳስተናል።**
**የዘንድሮን የመጋቢት መድኃኔዓለምን ክብረ በዓል ቅዳሜ መጋቢት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. [April 2, 2022] የአካባቢው ጳጳስ፥ ካህናትና ምዕመናን በሚገኙበት አንዲከበር መወሰኑን ስናበስራችሁ በታላቅ ደስታና ናፍቆት መሆኑን እንደምትገነዘቡ እርግጠኞች ነን።**
**በዚህ በሽታ ምክንያት እንደወትሮው ቤተክርስቲያን የሚመጡ ቁጥራቸው ቢቀንስም ስርዓቱ በየቤታችሁ በኢንተርኔት ስለሚደርሳችሁ በአካል ብንራራቅም በመንፈስ አንድነታችን አልተቋረጠም። በዚህ አስጨናቂ ጊዜም ሀላፊነታችሁንና ግዴታችሁን በመገንዘብ ለቤተክርስቲያኑ የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታችሁን አላቋረጣችሁም ። እጆቻችሁ ከያላችሁበት ተዘርግቶልናል። በዚህ ጭንቅ ጊዜ ላስታወሳችሁን ሁሉ የአምላክ በረከት አይለያችሁ፥ከቸነፈሩም እስከአሁን እንደጠበቃችሁ ወደፊትም ይጠብቃችሁ።**
**መድኃኔዓለም ፈቃዱ ሆኖ ጊዜው ደርሶ ዓመት በዓሉን እንድናከብር ሲጋብዘን ደግሞ ከወትሮው የተለየ ዓመታዊ የምስጋና ስጦታችሁን ይዛችሁ እንደምትቀርቡ አንጠራጠርም። እነዚያ ሰባ ሰገሎች የእየሱስን መወለድ ሰምተው በከዋክብት እየተመሩ ቤተልሔም ሲድርሱ ባዶ አጃቸውን አልቀረቡም። ማቴዎስ ምዕራፍ ሁለት ላይ በሰፊው ተተርኳል። ከያዙት ሳጥን እየከፈቱ ወርቅና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን አጅ መንሻ አንዳቀረቡ ተጽፏል። በዚህ የተቀደሰ ቀን ጥሪውን ተቀብላችሁ ስትመጡ ስጦታችሁን ይዛችሁ እንደምትመጡ እኛም ተስፋ እናደርጋለን። በጤንነትም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያቶች መምጣት የማትችሉ እንደተለመዳው ክብረ በዓሉን በስልክም ሆነ በዙም መከታታል የምትችሉ ሲሆን ስለታችሁን በሚከተለው አድራሻም ሆነ መንገድ ልትልኩልን ትችላላችሁ። መድኃኔዓለም ለዚያ ቀን ያድርሰን። በአንድነት ሆነን ስሙን እየጠራን ለማክበር ያብቃን።**
**ማሳሰብያ:**

> ***ለሎችም ሆነ ለራሳችሁ ጤንነት ሲባል የፊት መሸፈኛ ማስክ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ከወዲሁ ማሳሰብ እንወዳለን። መተቃቀፍና መሳሳም እንዲሁም መጨጋጋት እንዳይኖር ጥረት ማድረግም አስፈላጊ ይሆናል።***

**በቼክ/Check**
EOTCOS
302 East 206 st
Bronx, NY 10467

**Online: www.Medhanialem.org**
(የመጀመርያው ገፅ ላይ በግራ በኩል (ዶኔት)የሚለውን ንኩት)

**Dear Members and Supporters of Medhanialem**

**Due to the prevailing pandemic, for some of us, it has been a long time since we met at our beautiful Church for Sunday services. Our annual Savior's day celebration in the Spring has been put on hiatus for a couple of years now. However, we would like to share with you the good news of the resumption of Our Savior's annual day celebration on April 2, 2022 in the presence of neighboring Churches and Parishioners and the Bishop of the diocese. We anticipate a great celebration of praise and reunion of dear brothers and sisters. We invite you to be part of this celebration as well.**

**We also would like to remind you that this great day deserves a special thanks giving gift that befits the occasion. Reading Matthew Chapter 2, there is a narrative of men who travelled across a long distance to pay tribute to the baby Jesus in Bethlehem. They did not show up empty handed. They opened their boxes and gave gold and precious other items. We hope you will do the same as well just as you have been doing for the last two years of difficult period.**

**Those of you who for various reasons cannot show up on April 2, you may still follow the ceremony via Zoom and telephone. You may also send your gifts or offerings via the mail and online on the first page above. Thank you and may God bless you. We hope to see you all for the celebration.**

Reminder:

As a protection to ourselves and others, face covering masks are highly recommended. We also remind you to space apart with no hugging and keeping distances.

Respectfully,
The EOTCOS Board

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር፡
የመድኃኔዓለም የባለአደራ **ቦርድ**

## የ2014 የመድኃኔዓለም ክብረ በዓል ፕሮግራም

## 2022 Annual Medhanialem day Celebration Program

1 ከጠዋቱ 1 ሰዓት አስከ 4 ሰዓት ቅዳሴ (Mass 7am to 10 am)

2 የዕለቱ ወንጌል ትምህርት 4፡15 አስከ 4፡45 (Sermon of the day 10:15 to 10:45 am)

3 ከ4፡45 አስከ 5 ሰዓት መዝሙር (10፡45 to 11:00 am Church Choir Presentation)

4 ከ5፡10 አስከ 5፡40 (ዕርዳታ ማሰባሰብ ዝግጅት (11፡10 to 11:40 am Fund Raising)

5 ከ5፡45 እስከ 6፡30 (ታቦት ዑደትና ስንሥርዓት) 11፡45 to 12:30 am Procession of the Tabot)